# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ነሃሴ 24 ቀን 2007 ዓ. ም

## አዲስ ዓመት አዲስ ተስፋ

እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ በሰላም አደረሳችሁ በማለት ኢሕአፓ (አንድነት) ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም የአዲስ ዓመት ምኞቱን ይገልጻል።

የሰው ልጅ የሚኖረው በተስፋ ነውና አዲስ ዓመት ሲመጣ በድህነት ፊሰስ ውስጥ ያለው ሕዝብ ከቤቱ ጀምሮ እስከ ጎረቤቱ የዕለት ምግቡን እንዲሰጠውና በሰላም ውሎ በሰላም እንዲገባ ምኞቱን ይገልጻል፤ ሰፋ ሲል ደግሞ በአገርአቀፍ ደረጃ የመላው ኅብረተሰብ ችግር ተወግዶ አዲሱ ዓመት የተሻለ ነገር እንዲያመጣለት ሕዝብ የተሰፋ ምኞት የሚያልምበት ዘመን ነው። ሀብት ያለው ደግሞ ባለው ሀብት ላይ የበለጠ አፈራለሁ የሚል ተሰፋ ሰንቆ ለዕድገት የሚዘጋጅበትም ወቅት ነው። አዲስ ዓመት እንኳን ለሰው ልጅ ቀርቶ አዕዋፍም ልዩ ጣዕመ-ዝማሬ እያሰሙ በክረምቱ ምክንያት ሙቀት ወደ አለው አገር ተሰደው ከነበሩበት ወደ ነባር መኖሪያቸው የሚመለሱት እንኳን መሰከረም ሲጠባ ነው።

በሕዝባችን ስነልቦና ውስጥ  የአዲሱ ዓመት መጀመሪያ የሆነው የመስከረም ወር እጅግ በናፍቆት ይጠበቃል። ተማሪዎች በየዓመቱ በሰኔ ወር ትምህርት ቤታቸው ሲዘጋ ወደየመጡበት ቦታ በመመለስ የክረምቱን ወራት አሳልፈውና አሮጌውን ዘመን ተሰናብተው አዲሱን ዓመት በአዲስ መንፈስ አባባዬ ሆይን በደስታ እየዘመሩ አዲሱ የትምህርት ዘመን የሚጀምሩት በመስከረም ወር ነው።  ገበሬውም በክረምቱ ወራት ተጨፍግጎ የነበረውን አዕምሮውን አድሶ አዲስ የምርት ዘመን ለማግኘት ተስፋ ሰንቆ የሚነሳው በመሰከረም ወር ነው።  በመጥፎ ጠረን ታፍኖ ሕዝብ አላንቀሳቅስ ብሎ የነበረው የከተማ ቆሻሻ ሁሉ በክረምቱ ጎርፍ ተራርጎ መንገዶች ፀድተው፣ ሠፈር መንደሩ አምሮና ተውቦ የሚታየው በወርኃ መስከረም ነው።

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009

Phone: 202- 241 2078
Email: eprp-democratic@eprp-ihapa.com

ሰፋ ባለ መልኩም በአሁኑ ሰዓት በወያኔ አፈና ውስጥ የሚማቅቀው ሕዝባችን አዲሱ ዓመት ሰላምና ዴሞክራሲ የሚሰፍንበት ሁኔታ የሚፈጠርበትን፣ የተራበውም ጠግቦ የሚበላበትን መልካም ዓመት በጉጉት እንደሚጠብቅ እንገነዘባለን። ስለዚህም፣ በፖለቲካው ጎራ የተሰለፍን ድርጅቶች ሁሉ ይህንን ዕውነታ በመጭው አዲስ ዓመት እውን ለማድረግ አንድ ሆነንና ተጠናክረን ለበለጠ ትግል የምንነሳሳበት ዘመን እንዲሆን ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) ከወዲሁ መልካም ምኞቱን ይገልጻል። ምኞትን ብቻ መግለጽ ሳይሆን ደግሞ፣ የበለጠ የትግሉን ደረጃ ከፍ ለማድረግና ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ለዴሞክራሲና ለሕዝባዊ እኩልነት እንዲሁም ለሀገራችን ሉዓላዊነት ከሚታገሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ አገር ወዳድ ግለሰቦችና ስብስቦች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ለመታገል ቁርጠኝነቱን ጭምር ይገልጻል።

ሁሉም የተቃዋሚ ኃይሎች ተባብረው ይህን አፋኝና አገር አጥፊ ሥርዓት ማስወገድ እስካልቻሉ ድረስ ሕዝባችን መስከረም በጠባ ቁጥር የማይጨበጥ ተስፋ እየተመኘ እንዲኖር የፈረድንበት መሆኑን እያንዳንዳችን ልንረዳው ይገባል።

ስለዚህ ህወሓት/ኢህአዴግ ምንም እንኳን ውስጡ የተሸረሸረና ሕዝብ አንቅሮ የተፋው አገዛዝ ቢሆንም፣ በራሱ የተጠናከረ የስለላ ድርጅትና የመከላከያ ኃይል እንዲሁም ከራሳቸው ብሔራዊ ጥቅም በስተቀር ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ደንታ በሌላቸው የውጭ አገር መንግሥታት አጋፋሪነትና አይዞህ ባይነት እየተንቀሳቀሰ ዕድሜውን የሚገፋ ፀረ-ሕዝብ አገዛዝ በመሆኑ፣ ሊወገድ የሚችለው በተጠናከረ የተባበረ የሕዝብ ትግል ብቻ መሆኑን ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) ያምናል። ስለሆነም፣ ተቃዋሚ የአገር አንድነት ኃይሎች በሙሉ ለአዲሱ ዘመን ከምን ጊዜውም በበለጠ አዲስ ተስፋ ይዘንና ተጠናክረን በኅብረትና በትጋት እንድንታገል ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) አሁንም ጥሪውን ያቀርባል።

በተባበረ ክንድ አገራችንን ኢትዮጵያን ከጥፋት እናድናት!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009

Phone: 202- 241 2078
Email: eprp-democratic@eprp-ihapa.com